ኢትዮጵያችን

ኢትዮጵያችን ቅጽ 8 ቁጥር 1 መስከረም 06 ቀን 2016 ዓ.ም.

# "ይሸታል ሽሮ ሽሮ የማምዬ ጓሮ"

*(ኢትዮጵያችን ሀገር ወዳድ ወገኖች)*

በቅድሚያ እስከ ችግራችን፣ መከራችን ምኞት አይከለከልምና፣ ባህላችን ነውና እንኳን ወደ 2016 ዓ.ም. በሰላም አሸጋገራችሁ እንላለን። ብዙ አንመኝምና ዓመቱ ለሀገራችን አንድነት፣ ለሕዝባችን እንጀራ በሽሮ የመመገቢያ፣ ለሕጻናት ሻይ በዳቦ የማያጡበት፣ ሠራተኛው ከነችግሩ ወጥቶ የሚገባበት፣ ሥራ አጡ ተሸክሞ ተመስገን የሚልበት፣ አዛውንቶች ፀሎታቸው የሚሰማበት፣ ጋዜጠኞች ጽፈው የማይታሰሩበት፣ ዘረኞች ሳይታሰብ ብን ብለው የሚጠፉበት ዘመን ያድርግልን።

በትንሹ በአለፉት 50 ዓመታት ታሪካችንን ብንቃኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ረሃቡን ችሎ፣ መጨቆኑን ተቀብሎ፣ ኖሯል። ጭቆናና በደሉ ሲገፋም ገንፍሎ የወጣበት ወይም የተንቀሳቀሰበት ዘመን ቢኖር የየካቲቱ 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ነበር። በቀጣይበትም ጠንካራ አመራር በማጣቱ ዳግም በወያኔ/ህወሓት የተበላው የ1997 ዓ.ም. ሕዝባዊ ማዕበል ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ ቀይ ሽብር እና ጅምላ ፍጅት እየዬ ብሎ ሳያገግም፣ አልቅሶ ሳይወጣለት ወያኔ/ህወሓት ተረክቦት መከራ ማለት ምን እንደሆነ እስኪያንገሸግሸው ግቶታል። ከመጋቢት 2010 ዓ.ም. በጥገና ለውጥ ብቅ ያለው የዶር ዐብይ መንግሥት የሕዝቡን ስሜትና ፍላጎት በማስተጋባት ድጋፍ ቢቸረውም ውሎ ሳያድር እህል መሆኑ ተከሰተና የግፍ ጽዋውን ለሀገርና ለሕዝብ ይግት ጀመር። በዚህ አምስት ዓመት ጉዞ ይበልጥ እየተሰቃየ፣ እየተፈናቀለ፣ እየተሰደደና እየታረደ ያለው የአማራው ሕዝብ ነው።

እንደማንኛውም ብሔር/ብሔረሰብ ወይም ነገድ/ጎሣ አማራው የአገዛዙን ብልሹነት ቢገነዘብም ሳያስቸግር ሌሎችም እንደሚሉት የአገዛዙን የዘር ሕገ መንግሥት ተገን አድርጎ እየተጓዘ ነበር። ሆኖም የብልጽግና አገዛዝ ዋናው ዓላማ "ለኦሮሚያ የሆነች አዲስ ኢትዮጵያን መፍጠር" ነውና ለዚህ ጥርጊያ መንገድ አመቺ ይሆን ዘንድ ከዘር አማራ፣ ከሃይማኖት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ ከታሪክ ምኒልክ መዳከም ሳይሆን መወገድ ይኖርባቸዋል። "ታላቋ ኦሮሚያ" ማለት አማራ እየተቀጠቀጠ የሚኖርባት፣ የኢትዮጵያ ኦርትዶክስ ተዋህዶ እምነት የምትበረዝበት፣ ምኒልክና ዐድዋን መሰል ታሪኮች ተበርዘው ደብዛቸው የሚጠፋበት ነውና የዚህን ሂደት ለማሳካት የዶር ዐብይ አሕመድ ብልጽግና ቀስ በቀስ እያለሳለሰ የጀመረው ጉዞ ዛሬ ላይ አድርሶናል።

አማራው ከየትኛውም ክልል ወደ አዲስ አበባ እንዳይገባ ማዕቀብ ተደርጎበት በየአቅጣጫው ይዋከብ ጀመር። ለልማት እየተባለ ቤቱ የሚፈርሰው አማራው እየተመረጠ ሆነ፣ በየትኛውም ክልል ለዘመናት የኖረው አማራ ውጣልን እየተባለ የተገኘው ሁሉ ይታረድ፣ በጅምላ ይረሸን፣ ቤቱ በእሳት ይጋይ ጀመር። ልጆቹ መማር ካቆሙ ዓመታት አስቆጥረዋል። በወያኔ/ህወሓት ጥቃት ሲፈጸምበት እንዳላየ የሚያልፈው የአሁኑ አገዛዝ ይጠብቅ የነበረው ወያኔ ያዳከመለትን አማራ ድራሹን ማጥፋት ሆነና የተቀናጀ ተንኮላቸው ሳያስቡት ***"አማራ ፋኖ"***ን አጠንክሮ ዛሬ ዑ . . . ዑ . . . ሲያስኛቸው ይስተዋላል።

በመላው ሀገሪቷ ሲሰቃይ የኖረው አማራ ጥቃቱ አድማሱን እያሰፋ በአለበት አካባቢ ሳይቀር ከበባ እየተደረገበት በጅምላ ይጨፈጨፍ ጀመር። ወደ ኋላ ቢሄድ እየተከታተሉ መግደል፣ ወደ ግራ፣ ቀኝ ቢጓዝ እየጠበቁ መረሸን ሲሆን አማራጭ ያጣው አማራ ጉዞውን ወደፊት አድርጎ ከመተናነቅ አልፎ ማንነቱን እያሳየ ይገኛል።

በሁለት ዓመቱ የወያኔ/ህወሓት ጦርነት በሚዘገንን መልኩ ትምህርት ቤቶቹ፣ የሕክምና ማዕከላት፣ የተለያዩ ተቋማት የወደሙበት አማራ ክልል ከዚህ ሳያባራ እንዲቀጠቀጥ ተፈርዶበት በከበባ ውስጥ ወደቀ። አማራ መጥፋት ማለት "እንፈጥራታለን" የሚሉትን ኢትዮጵያን ማግኘት አንዱ እቅድ ነውና ለ"ኦሮሚያ ግንባታ" የአማራው ደምና አጥንት ማዳበሪያ ይሆን ዘንድ ተፈረደበት። ለዓመታት በመሠሪ ተንኮል ሲካሄድበት የነበረው ማዳከምና ማሽመድመድ በቂ አይደለምና በይፋ በመለፈፍ አከርካሪው በደንብ ይሰበር ዘንድ ጥቃቶች ሁሉ ወደ አማራ ዘር ጉዞ ቀጠሉ። በረሃብ ለመፍጀት ማዳበሪያ እንዳይገባለት ተደርጎ የሰብል ዓመቱን እህል ሳይዘራ እንዲኳትን ተደርጓል። በአዲስ አበባ ነዋሪ የሆነውን አማራ ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት "ሸገር ፕሮጀክት" በማለት በከበባ ታጥሮ እንዴት እንደሚጠፋ ቅድመ ዝግጅቱን የ***"አማራ ፋኖ"*** እንቅስቃሴና የሀገሪቷ የኑሮ ሁኔታ አዘቅት ውስጥ መግባት ጋብ ቢያደርገውም መርዘኛ ሂደት እንደሆነ መጠቆም እንወዳለን።

የ32 ዓመቱ አማራ ላይ የደረሰው ግፍና በደል በሀገራችን ኢትዮጵያ ታሪክ ገና ብዙ ይዘገባል። ዛሬ ነው የዮዲት ጉዲት የ40 ዓመት ቤተ ክርስቲያን፣ ሰማዕታትና አድባራት ውድመት ምን ያህል አስከፊ እንደነበር የምንገነዘበው። በቀጣይነት የ 16 ዓመቱ የግራኝ መሐመድ ወረራ ከወረራ የከፋ እልቂትና ውድመት ሀገራችንን እንዴት እንዳቆሰላት የሚሰማን። የ5 ዓመቱ የፋሺስት ጣልያን ወረራ በተለይ በአንድ ቀን ወደ ሰላሳ ሺህ ሕዝብ የተፈጀበትን የየካቲት 12 ሰማዕታት እልቂት ስናስታውስ በወቅቱ ከነበረው የአዲስ አበባ ሕዝብ ብዛትና የነዋሪ መጠን እውን የተረፈ ቤትና ሰው ኖሮ የሀገሪቷ ዳግም ማንሰራራት ተአምር እንጂ አሁን ባለው ወደ 7 ሚልዮን በሚቆጠር የአዲስ አበባ ነዋሪ ውስጥ አያርገውና በአንድ ቀን ሰላሳ ሺህ ሰው ብናጣ እንዴት እንደሚዘገንን ልብ እንበል።

ከላይ ያነሳናቸው ትንታኔዎች በመላ አብዛኛው አንባቢ የሚገነዘበውና የሚያውቀው ቢሆንም ግና ይህንን እያወቁ አሁን እየተካሄደ ላለው የ*"አማራ ፋኖ"* ከመከላከል አልፎ በመንግሥት ላይ የማጥቃት ሂደት ገባቸውም አልገባቸው ስለ ሰላም እና እርቅ ለሚደሰኩሩ የሀገራችን ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ መሆኑን ይገነዘቡ ዘንድና ትግሉ እዚህ ደረጃ ለምን ደረሰ? የሚለውን ለማስገንዘብ ነው።

ስለ ሰላም ምን ጊዜም ቢሰበክ የሚጠላ የለም። ሰላም ከሀገር አንጻር ምን ያመጣል? ምን ይፈጥራል? ማንም ሚከራከርበት ወይም የሚያጣው አይደለም። ሰላምን ጠልቶ ወደ ጦርነት ወይም ጸብ ፍለጋ የተጓዘው መንግሥት ነው ወይስ አማራ? በለሊት እየተከበበ የቤቱ ቆርቆሮ በላዩ ላይ የሚናደው አማራው አይደል እንዴ? ሻሸመኔ፣ አጣዬ፣ ወለጋ እየጋየ ያለው አማራ አይደል እንዴ? "ትጥቅህን ፍታ፣ ልዩ ኃይል አያስፈልግህም" ተብሎ ሊቀጠቀጥ የተደገሰለት አማራ አይደለም እንዴ? ኸረ ስንቱ. . .። እና አማራው ለኦሮሚያ ግንባታ ሲባል መጥፋት ነው ያለበት ወይስ . . .? እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለኦሮሚያ ግንባታ ስትል መጽሐፍ ቅዱሷን በርዛ በሶዶማውያን/በመናፍቃን መዋጥ ነው ያለባት ወይስ . . .? እና ለኦሮሚያ ግንባታ ሲባል ኢትዮጵያችን በነበር መወርወር ነው ያለባት ወይስ ጥንትም የደረሱባትን መከራዎች እንደተቋቋመች ሁሉ ይህንንም በልጆቿና በእምነቷ ጠንክራ ሀገርነቷን ማስቀጠል?

ሰሞኑን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሰላምና እርቅ ሲወረወር እናደምጣለን ሁሉም ያደምጣል። ማንም ሰላምን እርቅን የሚጠላ የለም። ከላይ በአጭር በአጭሩ ለመግለጽ እንደሞከርነው አሁን እየተካሄደ ያለውን በ*"አማራ ፋኖ"*ና በመንግሥት በኩል ያለውን ጦርነት ማን አመጣው? ***<u>አማራው እየታሰረ "እሺ"፣ እየተፈናቀለ "የባሰ አታምጣ"፣ እየተራበ "የነገን ማን ያውቃል?"፣ እየታመመ "እባክህ ፈጣሪ ሲቃዬን አታብዛው" ሌላም ሌላ እያለ ለበርካታ ዓመታት ተጉዟል። ይህም አልበቃ ብሎ በድህነቱ ተቀናበት፣ በዝምታው ጥርስ ተነከሰበት፣ በለቅሶው ተሳቀበት፣ በረሃቡ ተጨፈረበት፣ በቁስሉ እንጨት ተሰደደበት፣ በቤቱ እሳት ተለቀቀበት እና መውጫ ቀዳዳ ቢፈልግ፣ "አማራ ፋኖ" ቢል ያስደንቃል እንዴ?</u>***

ሀገሬ ኢትዮጵያ ማህተቤ ብሎ ያላየው መከራ የለም ሲበዛ ግን የግፉ ጽዋ ሲሞላ ከተነሳ እንደማይመለስ ያውቀዋልና "ቼ በለው!" ብሏል ዛሬ። አማራው "ቼ!" ሲል በታሪኩ አባዳኘው ፈረሱን ይጭናል፣ በእምነቱ ጊዮርጊስ ድረስልኝ ይላል፣ የነብዩ መሐመድ "ኢትዮጵያን አትንኳት" ብርታት ያወርሰዋል፣ በጀግንነቱ ቴዎድሮስን፣ በላይ ዘለቀን መሪው ያደርጋል። የአባዳኘው ፈረስ ከምዕራብ ምሥራቅ ከደቡብ ሰሜን እንደሚቃኝ *"አማራ ፋኖ"* ዛሬ መነሻው አማራ አድርጎ ወደ ምዕራብ ምሥራቅ ደቡብ ሰሜን እየቃኘ ይገኛል። በታሪኩ የአባት የእናቶቹ የዐድዋ ጀግንነት፣ የአምስት ዓመቱ የፋሺስት ተጋድሎ ደምና አጥንት ኢትዮጵያን እንዴት እንዳስቀጠለ ድቅን ይልበትና አሁንም "ደሜም ይፍሰስልሽ፣ ይከስከስ አጥንቴ፤ ለውዲቷ ሀገሬ ኢትዮጵያ እናቴ" ብሏልና ከዚህ ጉዞ የሚገታው አንድ ነገር ብቻ ነው ድል! ድል አድራጊነት!!!

አሁን *"አማራ ፋኖ"* እጅግ ባልተጠበቀ ሁኔታ የዶር ዐብይ አሕመድን የብልጽግና አገዛዝ እያርበተበተው ብቻ ሳይሆን እድሜውን ሊያሳጥረው እየገሰገሰ ይገኛል። በዚህ ሂደት ላይ ከመንግሥት ግራ መጋባት አንጻር በተጨማሪም ኢትዮጵያ ሁሌም እንደፈለጉ ይዘውሯት ይቃኟት ዘንድ የማይተኙልን ባዕዳን ሁሉ ስለ ሰላምና እርቅ ሲደሰኩሩ ይስተዋላሉ። በዚህም ስለ ውይይት ድርድር ሰሞኑን በአንዳንዶች ዘንድ የሚወረወሩና የሚንጸባረቁ ጉዳዮች በሚገባ መጤን ይኖርባቸዋል።

ስለ ጦርነት ሕይወት መቅጠፍ፣ ንብረት ማውደም፣ ኢኮኖሚን ማድቀቅ ትንተና ባይገባም አሁን ከአለው የብልጽግና አገዛዝ ጋር መነጋገር ወይም ድርድር ከተባለም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሥልጣን የሚለቅበት ብቻ ሳይሆን ያለው የዘር ሕገ መንግሥት የሚወገድበትን ይቀበል ዘንድ ማስገደድ በመሆኑ ይህ ደግሞ የሚሆነው *"አማራ ፋኖ"* የሥልጣን የበላይነቱን ሲቆጻጅ ነውና መዘናጋት እናድይፈጠር አበክረን ልንጠቁም እንወዳለን።

በድርድር ስም የቅርቡ የ1997 ዓ.ም. የቅንጅትን ታሪክ እንዳይደገም ልናሳስብ እንወዳለን። በመሆኑም ድርድርም ከተባለ፦

በወያኔ/ህወሓት በቀጣይነትም በብልጽግና አገዛዝ በትክክል ቁጥሩ ያልታወቀ ቢሆንም በሚልዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ተጠያቂ የመንግሥት ባለሥልጣናት ፍርድ መቅረብ ማለት ደማቸው ለፈሰሰው ፍትህን መጠየቅ አስታኮ፣

የሁለቱ ዘረኛ አገዛዞች ሕገ መንግሥት ያመጣው ጣጣ ለዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ሀገሪቷን ስለከተታት ሕገ መንግሥቱ ተሽሮ ትውልድ ተሻጋሪ ኢትዮጵያዊ ሕገ መንግሥት እስኪረቀቅ ድረስ ሀገሪቷ ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በተውጣጣ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ሥልጣኑን ይረከብ ዘንድ ማስገደድ የግድ አስፈላጊ ነው።

በርካታ ዝርዝር ሁኔታዎችን ማንሳት ቢቻልም መሠረታዊው የሀገሪቷ ችግር ከተነሳ ሌላው ሁሉ ሊስተካከል የሚችል ነው። ከዚህ ጋር አስቀድመን ልናሳስብ የምንፈልገው ***"አማራ ፋኖ"*** ለድል ከበቃ በኋላ የወያኔ/ህወሓት ሕገ መንግሥትን ይዤ እጓዛለሁ ካለ ኢትዮጵያን እንደማያድናት መቶ በመቶ መናገር እንችላለን። የዚህ ጊዜ ሀገራችን እፎይ እንዳትል ተፈርዶባታልና ትግሉ በሌላ መልኩ ይቀጥላል።

ስለ ሰላምና ምክክር ለምትሰብኩ በጥቅሉ ***"አማራ ፋኖ"***ን መነሳሳት ያመጣው ቆስቋሹ የዶር ዐብይ መንግሥት እንጂ አማራ አይደለምና ጥረታችሁ ባይናቅም ያበቃለት አገዛዝ እንደሆነ ተገንዝባችሁ ለተደናገጡት ባዕዳን ኃይሎች በር አትክፈቱ። ኢትዮጵያችን የእኛ መሆኗን ከተቀበልን የምናድናትም እኛው ነን። ለባዕዳን እየሰገዱ እዚህ ያደረሷት ወያኔና ያባባሰው ብልጽግና ከበቂ በላይ ነውና ለቀጣይ ተንበርካኪነት እንዳንዳረግ ልናስገነዝብ እንወዳለን። <u>*የሀገራችንን ታሪክ መለስ ብለን ብንቃኝ ባዕዳን እኛን ማጥቃት የጀመሩት ጥንት ሲሆን፣ ሚያግዙን መስለው ሲያጠቁን፣ ሚያክሙን መስለው ሲያሳምሙን፣ ሚመግቡ መስለው ሲያስርቡን፣ ሚረዱን መስለው ሲያሰድዱን፣ ሚያስተምሩን መስለው ሲያደነቁሩን፣ ሚያበቅሉልን መስለው አረም ሲተክሉብን፣ አንድ ሰጥተው ሺህ የሚዘርፉን፣ ሃይማኖት ብለው ግብረሰዶም ያበቀሉብን፣ ሥልጣኔ ብለው ፍቅራችንን የበሉብን፣ ትግል ብለው ትውልድ ያስጨረሱብን፣ ሌላም ሌላ ናቸውና ለኢትዮጵያችን ሀኪሟም ፈዋሿም ከፈጣሪ ጋር እኛውና እኛው ብቻ ነን።*</u>

<u>*በሀገር ቤት ሕጋዊ ውክልና ይዛችሁ ለምትንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ፦*</u> በተለይ ለኢትዮጵያ ሀገራችንን ሕዝባችን የዴሞክራሲ ጭላንጭል ፈነጠቀ ብላችሁ ወደ ሀገር ገብታችሁ የበኩላችሁን አስተዋጽዖ እያደረጋችሁ ያላችሁ በአጭሩ የምንላችሁ ትግል በፍርሃት አይሆንም! ትግል መስዋዕትነትን ይጠይቃል፡ የያዝነውን ሕጋዊነት እናጣለን በሚል ከመንግሥት ከመጋጨት በመልመጥመጥ አሳፋሪ ታሪክ መድገም ውስጥ እንዳትዘፈቁ ልናሳስብ እንወዳለን።

አዎ! መንግሥት ሲያዩት አስፈሪ ነው። ግና በማትጠብቁት መልክ ደግሞ ገለባ ነው። ለዚህም ነው በዚህ 50 ዓመት ታሪካችን እስከመጨረሻዋ ሰዓት ". . .ተቆጣጠርኩት፣ ትንሽ ርዝራዦች፣ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን፣ ጥቂት ወንበዴዎች፣ የተቃጣውን መከትን፣ የድጋፍ ሰልፍ ተደረገልን፣ ሕዝቡ ተቃዋሚዎችን አወገዘ፣ ሕገ መንግሥት ለመናድ. . ." ሳይል፣ ሳይፎክር፣ ሳያቅራራ የተወገደ አገዛዝ የለምና የብልጽግናም አገዛዝ ጉዞው ወደ መወገድ እንደሆነ አንጠራጠር። ያገኘውን ዕድል አጣጥሞ የበላ አገዛዝ ቢኖር የጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዐብይ አገዛዝ ነው። ለራሱ ሲል ሊጣፍጥ አልቻለምና ሕዝብና ሀገር ድንጋይ ከሆነባቸው ስለሰነባበተ መወርወር ያለበት አገዛዝ ሁኗል።

***"አማራ ፋኖ"*** የመጨረሻ አማራጭ ይህን አገዛዝ ብቻ አይደለም ዘረኝነትን ከሥሩ ለመንቀል እየተፋለመ፣ እየተዋደቀ፣ አጥንቱን እየከሰከሰ፣ ደሙን እያፈሰሰ ባለበት በዚህ ወሳኝ ምዕራፍ ስለ ሰላም አስፈላጊነት በመደስኮር ሌላውን ጦረኛ ለማድረግ አንደበታችን ባይበረክት ለማስገንዘብ እንወዳለን። ለዴሞክራሲና ለሕዝብ መንግሥት ግንባታ ሲባል መሣሪያ አንሥቶ በገጠርም ሆነ በከተማ የተፋለመ ኃይል ለምን መሣሪያ እንዳነገበ ቢጠየቅ "የሰላም በሮች ሁሉ ስለተዘጉ" መልሱ ነውና ሌላውን ጦረኛ ብሎ ለማውገዝ "እውን የሞራል ብቃቱ ይኖረናል ወይ?" ብሎ መጠየቁ አግባብነት እንዳለው ልንጠቁም እንወዳለን።

ሰላማዊ ትግልም ከሆነ እየተፋለመ ያለውን ***"አማራ ፋኖ"***ን ለቀቅ አድርጎ አሁን ሀገሪቷ በገጠማት የኑሮ ውድነት ብቻ እጅግ የገዘፈ የከተማ ሕዝባዊ እምቢተኝነት በማነሳሳት ኢትዮጵያችንን ለማዳን ብትረባረቡ ይመረጣል። ዛሬ በዚህ አዲስ ዓመት 2016 ዓ.ም. <u>**"ይሽታል ዶሮ ዶሮ የእማምዬ ጓሮ"**</u> ሳይሆን ይሸታል ሽሮ ሽሮ ከተባለለትም የሚደንቅ ነውና እባካችሁ ወቅቱንና ጊዜውን ያገናዘበ ትንታኔ በመስጠት ይልቅስ ደሙን ለሚያፈሰው፣ አጥንቱን ለሚከሰክሰው ***"አማራ ፋኖ"*** በከተማው ሕዝባዊ እምቢተኝነትን በማንቀሳቀስ አግዙት እንላለን።

***"አማራ ፋኖ"*** ነገ ወደድል ሲቃረብ አይደለም እንምራው፣ ሽግግር መንግሥት፣ ሰላማዊ ሰልፍ፣ ለማለት መሯሯጥ። ጊዜና ትግል እጅግ እየቀደማችሁ ሂዷልና ድረሱበት ወይም በአግባቡ ተከተሉት።

ሌላው ስለ ምርጫ ፖለቲካ ከእንግዲህ ሊታሰብም ሊወራም የሚከጀልበት ወቅት ላይ አይደለንም። በምንም መልኩ የብልጽግና ኦሮሙማ አገዛዝ እንደ ወላጁ ወያኔ/ህወሓት የምርጫ አጃቢ ፈላጊ እንጂ ሥልጣን መልቀቅ አይደለም አያጋራም። ሌላው ቀርቶ ከቅርቡ 1997 ዓ.ም. ዘመነ ቅንጅት ትርይት መማር ያልቻለ የፖለቲካ ድርጅት ችግር አለበት ወይም በሁለት ቃላት "ፈሪ" ነው።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቅልን!!! መስከረም 06 ቀ 2016 ዓ.ም. (September 16, 2023)